# አላርፍ ያሉት የአስመራው ቡድን የሽብር እጆች

**ቻላቸው በላይነህ**

**03-13-15**

የኢፌዴሪ ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ጄኔራል አሰፋ አብዩ በትናንትናው ዕለት እንደተናገሩት የኤርትራ መንግስት የምርጫውን ሂደት ለማደናቀፍ ጥረት ማድረጉን ተናግረዋል።

በዚህም ራሳቸውን 'ግንቦት ሰባት፣ አርበኞች ግንባር፣ ደምህት፣ ኦብነግና አልሸባብ' እያሉ የሚጠሩ የሽብር ቡድኖችን በቀጥታና በተዘዋዋሪ በማገዝ ምርጫው ሰላማዊ፣ ፍትሐዊና ተዓማኒ እንዳይሆን ቢጥርም በፀጥታ ኃይሎች ትብብር እኩይ ሴራው በፀጥታ ኃይሎች ትብብር መክሸፉን ገልፀዋል። የፌዴራል ፖሊስም የምርጫው ሂደት በሰላማዊ ሁኔታ እንዲከናወን አስፈላጊውን ጉዳዩች ሁሉ እያከናወነ መሆኑን ተናግረዋል።

እርግጥ የጥይት አረርን እንደ ዕጣን ካላሸተተ ውሎ የማያድረው፣ ግብረ- ሽበራን እንደ እለት እንጀራው የተያያዘውና "እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል" በሚል የሞኝ ብሂል ከራሱ ፃዕረ-ሞት ጋር ትንቅንቅ የሚያደርገው የአስመራው ቡድን፤ ዛሬም ድረስ በሆን ቀጣነውን በማተራመስ አላርፍ ያሉትን የሽብር እጆቹን አልሰበሰበም። ጦርነትን እንደ ንግድ የሚቆጥር ጥገኛ ቡድን በመሆኑም ከዚህ ዓይነቱ የትርምስና የሽብር ፈታውራሪነት ተግባሩ ይቆጠባል ተብሎ አይታሰብም።

እንደሚታወቀው ገና ከጅምሩ ሻዕቢያ የኤርትራን ነፃነት ከማረጋገጥ አልፎ፡ በዚያች ሀገር ማህበራዊ ፍትህን እንደማያነግስ በእርግጠኝነት የሚናገሩ ሰዎች በርካታ ነበሩ፡፡

እርግጥም የእነዚህ ግለሰቦች ‹‹ትንቢት›› ከመሬት ተነስቶ የተባለ አልነበረም— ከነባራዊ የድርጅቱና የመሪዎቹ ሁኔታ የተነሳ እንጂ፡፡ ለምን ቢባል፡ አነ አቶ ኢሳያስ ከሳህል ተራራ ጀምረው ይመሩበት የነበረው አካሄድ በጥገኝነት ላይ የተንጠለጠለ እንዲሁም በቀቢፀ ተስፋና በእልህ የሚዋተት የጦረኝነት አባዜ ስለነበር ነው፡፡

እንዲህ አይነቱ ፀረ-ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ደግሞ "ያደቆነ ሰይጣን ሳያቀስ አይተውም" እንዲሉ ዓይነት በመሆኑ፤ ከኤርትራ ነፃነት በኋላ የስልጣን ኮርቻ ላይ የተቀመጠው የሻዕቢያ ቡድን በሀገር ውስጥ ህዝቡን ወደ ተሻለ ማህበረሰብ ከማራመድ ይልቅ፣ በላዩ ላይ ከፍተኛ የአፈና ቀንበር ነው የጫነበት፡፡ በሚከተለው ብልሹ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ አመራርም ሀገሪቱን ወደማያባራ ቀውስ ውስጥ ከትቷታል፡፡

የኤርትራን ህዝብ እንደ ብረት ቀጥቅጦና እንደ ሰም አቅልጦ በመግዛት ላይ የሚገኘው የህግዴፍ ቡድን፤ በሀገረ-ኤርትራ ህገ-መንግስት እንዳይኖር፣ ነፃ ፍርድ ቤት እንዳይሰየም፣ ምርጫ እንዳይካሄድ፣ የግል ፕሬስ እንዳይፈጠር ባለፉት 20 ዓመታት ተግቶ ሰርቷል፡፡

የተጣባውን የጥገኝነት ተውሳክ በዚያች ሀገር ውስጥ እውን ለማድረግም በአደባባይ ወጥቶ መግለጫ እስከመስጠት የደረሰ ጉደኛ መንግስት ነው፡፡ ለዚህም በአንድ ወቅት አምባገነኑ ኢሳያስ ለመገናኛ ብዙሃን "ለኤርትራ ዴሞክራሲ፣ መድበለ ፓርቲ ስርዓትና ምርጫ የሚባሉት ነገሮች አያስፈልጓትም፡፡ አሁን ያለው ስርዓት ትክክለኛ አማራጭ ነው" በማለት ዓለም የተቀበላቸውን ዴሞክራሲያዊ አሰራሮችን እንደ ተላጠ የኤሌክትሪክ ሽቦ እንደሚፈሯቸው በግልፅ የተናገሩትን ሃቅ ማውሳት ይቻላል፡፡

ይህ ሁኔታም "ከነፃነት በኋላ ዲሞክራሲና ፍትህ ይመጣል" ብሎ የጠበቀው የዚያች ሀገር ምስኪን ህዝብ፤ በአቶ ኢሳያስ የተደገሱለት ሀገሩ የዲሞክራሲና የሰብዓዊ መብት ምድረ-በዳ መሆኗን በመገንዘቡ፤ ለህግዴፍ የሰጠውን ይሁንታ ነፍጎ የፕሬዚዳንቱን ዕድሜ እንዲያሳጥርለት መመኘት እንዲጀምር አድርጎታል፡፡

ይህን ተከትለው ለአቅመ አዳም ያልደረሱና አዛውንቶች ሳይቀሩ የአቶ ኢሳያስን የግፍ በትር በመፍራት ሀገራቸውን ለቀው እየተሰደዱ ነው—"ማምሻም ዕድሜ ነው" እንዲል የሀገራችን ሰው፡፡

በሻዕቢያ አመራር በትምህርት የማደግ ህልማቸው እንዲሞት የተደረጉት የሀገሪቱ ወጣቶችም ቢሆኑ "ሳዋ፣ ኪሎማና ማይነፍሂ" የተባሉ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ጣቢያዎች ከመግባት፣ ለኬላ ጠባቂዎች በሙቶ ሺህ የሞቆጠር ናቅፋ በመስጠት የጎረቤት ሀገሮችን ድንበር እያቋረጡ በመሸሽ ላይ ይገኛሉ፡፡

እርግጥም ቀለምና ወረቀት አዋህደው ያቺን አዲስና ትንሽ ሀገር ሲያሳድጓት የሚችሉ ወጣቶች፤ ዛሬ በምሽግ ውስጥ እንዲውሉ ሲፈረድባቸው፣ በየወታደራዊ ማሰልጠኛው ጠብ-መንጃ ሲፈቱና ሲገጥሙ እንዲሁም ሰልፍ እንዲለማመዱ ሲደረጉ ብሎም "ዋርሳይ ይከአሎ" እየተባለ በሚጠራው ዘመቻ መንገድ እንዲሰሩ ብሎም የጄኔራሎችን እርሻ እንዲያለሙ ጉልበታቸው ሲበዘበዝ ጨርቄን ማቄን ሳይሉ ከ"ከአቶ ኢሳያስ ሀገር" መጥፋታቸው የሚያስገርም አይሆንም፡፡

በዚህ ፅሁፍ አቅራቢ እምነት፡ የኤርትራ መንግስት በትንኮሳ ላይ ትንኮሳ እያከታተለ የሚፈፀምበት ዋነኛው ምክንያት፤ እንደ እሳተ-ገሞራ ለመፈንዳት የተቃረበውን ውስጣዊ ተቃውሞ ያረገበ መስሎ ስለሚታየው ነው፡፡

የአቶ ኢሳያስ አስተዳደር በየጊዜው ወደ ኢትዮጵያ የሚልካቸው እንደ ኦነግ፣ ኦብነግና ግንቦት 7 የመሳሰሉ አሸባሪዎች ውጤት ሊያመጡለት ስላልቻሉ፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ቅጥረኞችን በማሰልጠንና በማስታወቅ የሀገራችንን መልካም ስም ለማጉደፍ በቀቢፀ- ተስፋ እየተራወጠ ይገኛል፡፡ ግና ኮሚሽነር ጄኔራሉ እንዳሉት ይህ ተግባሩ በሀገራችን ፀጥታ ሃይሎች ትብብር ያሰበውን ሳያሳካ እንዲሁ በመባዘን ላይ ይገኛል።

የኤርትራ መንግስት ተላላኪዎችንና ቅጥረኞችን እየፈለፈለ፣ አንድን ሀገር ተተናሎ ሲያበቃ በምላሹ ሀገራቱ ጣታቸውን ወደ እርሱ ሲቀስሩ፣ ህዝቡን “እገሌ የሚል ሀገር ሊወርህና ነፃነትህን ሊያሳጣህ ነው” በሚል ፕሮፓጋንዳ ለማወናበድና ለጊዜውም ቢሆን ለህዝባዊ ተቃውሞው ፋታ መውሰጃ ይጠቀምበታል፤፡

በተለይም ራሱ የተከተለው ፖለቲካዊ-ኢኮኖሚ አካሄድ መልሶ ራሱን ጠልፎ እንደጣለው ባለመገንዘቡ፤ ለውድቀቱ ምክንያት ኢትዮጵያ እንደሆነች አድርጎ በማቅረብና በሀገራችን ላይ በትንኮ ላይ ትንኮ እየፈጸመ መቀጠልን እንደ አማራጭ ወስዷል፡፡

እንደ እውነቱ ከሆነ አስመራው መንግስት የሽብር አዝማችና ኢጋፋሪ ሆኖ የቀጠለው በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት አከርካሪው ተመትቶ ከተሰባበረ በኋላ ነው ማለት ይቻላል፤፡ በኤርትራ ውስጣዊ አቅምና ፀጋዎች ከመተማመን ይልቅ፣ የጎረቤት ሀገሮችን ሃብት በጥገኝነት ዓይኑ ያማትር የነበረው የአቶ ኢሳያስ ቡድን፣ ማጣፊያው ሲያጥርበት በአንድ ወቅት “ሀገራችንን ሲንጋፖርና ታይዋን አድርገን ምርቶቻችንን ወደ ውጭ አንልካለን” እንዳላለ፡ ዛሬ ሽብርንና ትርምስን አስመራ ውስጥ እያመረተ ወደ ጎረቤት አገር መላክ ሁነኛ ስራው ሆኗል፤፡

በዚህም የሱዳንና የጅቡቲ “አማፂዎችን” እንደ ሀገር ውስጥ ምርት በየወታደራዊ ማሰልጠኛው እያመረተ በመላክ ላይ ይገኛል፤፡ ራሳቸውን ኦነግ፣ ኦብነግ፣ ግንቦት 7 ወዘተ እያሉ የሚጠሩ የሀገራችንን አሸባሪዎችንም እየመለመለ፣ እያሰለጠነ፣ እያስታጠቀና እያሳረገ ለማስገባት ሞክሮ ባይሳካለትም፤ የጥፋት እጆቹን እስካሁን ድረስ ከኢትዮጵያ ላይ ሊያነሳ አልቻለም፡፡

ሻዕቢያ በሀገረ ሶማሊያ ውስጥ አክራሪዎችን ከማሰልጠንና ከማስታጠቅ አልፎ ወታደሮቹን ልኮ እስከ መዋጋት ደርሷል፡፡ በዚህም የገዛ ዜጎቻቸውን እጅና እግር የሚቆርጡ አሸባሪዎችን እየረዳ ያቺን ሀገር የደም ምድር በማድረግ ረገድ የበኩሉን አሉታዊ ድርሻ ተጫውቷል፡፡ በቅርቡም አል-ሸባብ ለተሰኘው የሽብር ቡድን የስልጠና፣ የሎጀስቲክስና የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ የግብረ-ሽብራ ፊታውራሪነቱን በጠራራ ፀሀይ አረጋግጧል፡፡

ከሽብር ተግባር ጋር የካቶሊክ ጋብቻ የፈፀመው የአቶ ኢሳያስ መንግስት፤ እኩይ ሴራውን በምስራቅ አፍሪካ ተወዳድሮ ያገኘው “ክፍት የስራ ቦታ” ይመስል ‹ሞቴን ከአሸባሪዎች ጋር ያድርገው› ብሎ ተገዝቶ ከማለ ሰነባብቷል፡፡ ታዲያ ይህን ተግባሩን በአሁኑ ወቅት እያደረገ ካለው አፍራሽ ድርጊት አኳያ ስንመዝነው፤ ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ከአንድም ሁለቴ ከጣለበት ማዕቀብ እንኳን የሚማር አይመስልም፡፡

እንደሚታወቀው በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የፀጥታው ምክር ቤት የኤርትራ መንግስት በኃይል ከያዘው የጅቡቲው ራስ ዱሜራ ግዛት እንዲወጣ እንዲሁም የሶማሊያ አሸባሪዎችንና ጽንፈኞችን መርዳቱን እንዲያቆም ሲጠይቀው፣ ‹እምቢኝ አሻፈረኝ› በማለቱ የመጀመሪያውን የመሳሪያ ዝውውር፣የባለስልጣናት ጉዞና ሌሎች ማዕቀቦችን

ጥሎበታል፡፡ ይሁንና ዓለም አቀፉን ህግና ስርዓት በይፋ የሚዘልፉት አቶ ኢሳያስ፣ የፀጥታውን ምክር ቤት ማዕቀብ ከቁብ ሳይቆጥሩ በሽብር አዝማችነታቸው እነሆ ዛሬም ቀጥለውበታል፡፡

ሆኖም የምስራቅ አፍሪካ የልማት በየነ መንግስታት ባለስልጣን (ኢጋድ) እና የአፍሪካ ህብረት የአስመራው ቡድን የቀጠናው ተናዳፊ ኃይል መሆኑንና ያካባቢውን ሰላምና መረጋጋት ማደፍረሱን ለጸጥታው ምክር ቤት በማመልከታቸው፤ ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ የኤርትራንና የሶማሊያን ሁኔታ የሚያጣራ አካል መድቧል፡፡

አጣሪ ቡድኑም ባደረገው ጥልቅ ጥናት የአስመራው አስተዳደር የአካባቢው ሰላም ጠንቅ መሆኑን አረጋግጧል፡፡ የህግዴፍ መንግስት ቀደም ሲል የተጣለበትን የመሳሪያ ዝውውር ማዕቀብ በመተላለፍ ለአል-ሸባብ መሳሪ እንደሚያቀብል፣ የጎረቤት ሀገሮችን ፀረ-ሰላም ኃይሎችና አሸባሪዎችን ጉያው ስር ወሽቆ ሀገራቱን እንደሚያውክ የቡድኑ ሪፖርት አረጋግጧል፡፡

ናይሮቢ የሚገኘው የኤርትራ ኤምባሲ ተቀዳሚ ስራው ድፕሎማሲ ሳይሆን በሃዋላና በደሃብሺል የገንዘብ ማዘዋወሪያዎች አማካኝነት በአል-ሸባብ የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ እንዲሁም ለሽብተኛ ቡድኖች ሽፋን የመስጠት ተግባር መሆኑን አጣሪ ቡድኑ ደርሶበታል፡፡

ይሁንና የአስመራው አምባገነን መሪ በጀሌዎቻቸው አማካኝነት የአንድን ሉዓላዊት ሀገር ድንበር ጥሰው ሽብር የሚፈፅሙበት አካሄድ አንድ ቦታ ላይ መገታት ይኖርበታል፡፡

የኤርትራ መንግስት በባህሪው ለትዕግስት ቦታ የሚሰጥ ባለመሆኑ፤ ከዚህ ፀያፍ ተግባሩ እንዲታቀብ የመንግስታችን የተለመደው አስተዋይነትና ብቃት ያለው የአመራር ክህሎት ታክሎበት ተመጣጣኝ እርምጃ ያስፈልገዋል ባይ ነኝ፡፡ እናም በዚህ ፅሁፍ አቅራቢ እምነት አቶ ኢሳያስ የባሩድ ሽታን እንደ ሀሺሽ “የመጀንጀን” ሱስ የተጠናወታቸው በመሆኑ፣ እርሳቸው “በሚገባቸው ቋንቋ” አናግሮ ተገቢ ትምህርት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

እንደሚታወቀው ሻዕቢያ በሳህል ተራራዎች ውስጥ በመሸገበት ወቅት መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ያገኘው የነበረው ዳረጎት፤ ስልጣን ከያዘም በኋላ ቢሆን ይህን መስሉን ገቢ የአካባቢው ሀገሮች አድራጊ ፈጣሪ ሆኖ ለማግኘት ይቋምጥ ነበር—ፍላጎቱ ከንቱ ቅዠት ሆኖ ቀረ እንጂ፡፡

እናም በአፍሪካ ቀንድ ውስጥ ጥቅማቸውን ለማስከበር የሚንቀሳቀስ አንዳንድ ሀገራትን በቀጣናው አውራ ስለሆንኩ፣ ከእኔ ጋር ጥሩ ግንኙነት ብትመሰርቱ ትጠቀማላችሁ በማለት ኪራይ ለመሰብሰብ ያልፈነቀለው ድንጋይ አልነበረም፡፡

ግና ምን ያደርጋል?! ከኢትዮጵያ ጋር ያደረገውና በገዛ እጁ የከፈተው ጦርነት ራሱን ሰቅሎ ከነበረው የህልም ዓለም ማማ ላይ እንዲወርድ አደረገው፡፡ በዚህም እስከዛሬ ድረስ ሀገራችንን በደመኛ ጠላትነት ፈርጆ፤ ፀረ-ሰላምና አሸባሪ

ኃይሎችን እንደ አሮጌ ዕቃ ከወዳደቁበት ለቃቅሞ እያነሳ ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ መልካም ገፅታዋን ማጥቆር እምቡር እምቡር እያለ ነው፡፡

በዚህ ጽሁፍ አቅራቢ እምነት የአቶ ኢሳያስ መንግስት ያልተገነዘበው ትልቅ ጉዳይ አለ፡፡ ይኸውም እርሱ በየጊዜው ለሚጎነጉነው የሽብር ሴራ እንደ ነብር ጭራ ከያዘው ፈጣንና ተከታታይ ልማታዊ ዕድገት የሚዛነፍ መንግስትም ይሁን ህዝብ አለመኖሩን ነው፡፡

የሀገራችን ህዝብና መንግስት የሻዕቢያ ኢኮኖሚ በየጊዜው ከድጡ ወደ ማጡ እየተንሸራተተ መግባቱን ብቻ ሳይሆን፤ እንደ መንግስትም ህልውናው አጠራጣሪ ሁኔታ ላይ መድረሱን ይረዳሉ፡፡ አርግጥም ከራሱ የሞት መንፈስ ጋር ትንቅንቅ እያደረገና በቀቢፀ-ተስፋ ቀሪ ዘመኑን ለመዳከር የወሰነ መንግስትን እብደት እያዩ እርሱ በመረጠው ጎዳና ላይ አብረውት አይሮጡም።

ይሁንና ይህ ማለት ግን፤ የጀመሩትን የዕድገት ጎዳና ለማደናቀፍ ሀገራቸው ውስጥ በማን አለብኝነት የሽብር ተግባርን አከናውናለሁ የሚል ኃይልን ዝም ብለው ያያሉ ማለት አይደለም፡፡ ከብዙ ትዕግስት በኋላ፤ ሰላማቸውን በማስጠበቅ ልማታቸውን ያለምንም እንከን ለማከናወን አስፈላጊ ነው ያሉትን እርምጃ ከመውሰድ ወደ ኋላ እንደማይሉ መገንዘብ ይበጃል፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት እስከዛሬ ድረስ የአስመራውን አስተዳደር የጠብ-አጫሪነት ተግባር ዓለም አቀፉ ህግ የሚቅደውን አግባብ ተከትሎ ችግሩን ለመፍታት ጥረት አድርጓል፡፡ ሌላው ቀርቶ በአንድ ወቅት የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ልዩ ጉባኤን ለመበጥበጥ የኤርትራ መንግስት የሞከረውን ፍጹም ፀረ-ህዝብ ድርጊት እንኳን ለዓለም አቀፉ ማህበረተሰብ አሳልፎ ከመስጠት ውጪ የወሰደው እርምጃ የለም፡፡ ይህም መንግስት ምን ያህል በህግ እና በህግ ብቻ እንደሚገዛ በተግባር አረጋግጧል፡፡

እርግጥ የአስመራው ቡድን የሚያሰማራቸው ቡድኖች ማንነታቸው በገሃድ የሚታወቅ ነው። ጥቂቶቹን ለአብነት ያህል እናንሳ። እርግጥ የኢፌዴሪ የህዝብ ተወካዩች ምክር ቤት በአሸባሪነት የሰየማቸው አምስት ድርጅቶችን በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በመደገፍ ሀገራችን የተያያዘችውን የሠላም፣ የልማትና የዴሞክራሲን ትሩፋቶች ለማደናቀፍ ሲጥር ቆይቷል-ምኞቱ ጉም የመዝገን ያህል ቢሆንም፡፡

ዛሬ በኢሳያስ አፈወርቂ የሚመራው የአስመራው ነውጠኛ መንግስት፣ በወታደራዊ ጡንቻና በጥገኝነት አስተሳሰብ ደዌ የተለከፈው፣ ከአራት አስርት ዓመታት በፊት ሰው በማይኖርባቸው የሳህል ተራሮች ላይ በመሸገባቸው ጊዜያት እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በዚህ አስተሳሰቡም ሀገሪቱ ውስጥ "መንግስት" እስከ መሰረተበት ጊዜ ድረስ በተጠናወተው የወታደራዊነት አምልኮ ራሱን በራሱ በመካብ "ከእኔ ወዲያ ጀግና ላሳር" በማለት ራሱን ከሳህል ተራሮች በላይ ቆለለ፡፡ "አይበገሬ ነኝ" በሚል በፈጠረው የልቦለድ ዓለም "ማንነቱ" እየተጽናናም፣ በራሱ የዳንስ ስልተምት

ይውረገረግ ጀመር፡፡…እርግጥ ይህን የወታደራዊነት አባዜውን ኤርትራ ውስጥ መንግስት ከመሰረተ በኋላ ይተወዋል የሚል አስተሳሰብ በበርካታ ሰዎች ውስጥ ነበር - እንዲያው በነበር ቀረ እንጂ፡፡ መንግስት መስርቶ ለጥቂት ዓመታት ብቻ "እረፍት የወሰደው" የአቶ ኢሳያስ ቡድን፣ ድንገት የሳህል ተራራው የጀብደኝነት አብሾው ተቀስቅሶበት፣ በአመዛኙ የሠላም ድባብ ሰፍኖበት የነበረውን ምስራቅ አፍሪካንና ከባቢውን ለማወክ ማጓራት ጀመረ፡፡ የተጣባውን ይህን የጀብደኝነት ተውሳክ የሚያሸር መድኃኒት ፍለጋም ወደ የመን፣ ሱዳን፣ ኢትዮጵያና ጅቡቲ አቀና፡፡…

…"ዘራፍ እኔ የጀብደኝነትና የጥገኝነት አሽከር!" እያለ ወደ እነዚህ ሀገራት የተመመውና በቅጽል ስሙ "ቅሌት ምሱ" እየተባለ የሚጠራው የኢሳያስ ጦር፣ ዘመናዊውን ዓለም በጫካ ህግ የሚያስብ በመሆኑ የሳህል ተራራው ጀብደኝነቱ "ከነበር" ሊያልፍ አልቻለም፤ አልቀናውም፡፡ ዓለም በህግና በሥርዓት የሚመራ እንደመሆኑ መጠን፣ ገሚሱ በፍርድ ቤት ክርክር፣ አንዳንዱን በሸምጋይ ሀገራት አማካኝነት ቀሪውና በሀገራችን ላይ ያደረገው ወረራ ደግሞ ራሱ በመረጠው የወታደራዊነት መንገድ አከርካሪው ተሰብሮ አስመራ እንዲከትም ተደረገ፡፡

ታዲያ ከኤርትራ ህዝብ ፍላጎትና እምነት ውጪ በሌሎች አንጡራ ሀብት ላይ ተንጠላጥሎ የጥገኝነት ኮሮጆውን ለመሙላት እንደ አበደ ውሻ ከሀገር ሀገር ሲክለፈለፍ የነበረው የሻዕቢያ ቡድን፣ የሃፍረት ካባን ተከናንቦ ቤተ-መንግስቱ ውስጥ መሽጎ ብቻ ቁጭ አላለም፡፡ ይልቁንም ሀገራቱን ሊያዳክም የሚችል አዲስ የትርምስ ስትራቴጂ ይዞ ብቅ አለ፡፡ ይህም ቀደም ሲል አጎራባቾቹን በመውረር በምዕራባዊያን ዘንድ የቀጣናው "አውራ" ተደርጎ እንዲታይ ያደረገው ከንቱ መፍጨርጨር ስለከሸፈበት "እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል" በሚል ብሂል በሽብር ማናወጥ ነው፡፡

የኢሳያስ ነውጠኛ ቡድን በየመን የመንግስት አማጽያን በማደራጀትና በማስታጠቅ፣ በሱዳን የዳርፉር ግጭት እንዲባባስና በሀገሪቱም የምስራቃዊ ክፍል "ቤጃ" የሚባል አማፂን በመፍጠር፣ በጅቡቲ "ፍሩድ" የተሰኘ ተቃዋሚን በማደራጀት እንዲሁም የሀገራችንን አሸባሪዎች እንደ አሮጌ ዕቃ ከወዳደቁበት ለቃቅሞ በማሰልጠን፣ በማስታጠቅና አስርጎ ለማስገባት በመሞከር የትርምስ ስትራቴጂውን ገቢራዊ ማድረግ ጀመረ፡፡

እንደ ቀድሞው የግብጽ መንግስት ያሉ አንዳንድ ኃይሎች ከራሳቸው ፍላጎት በመነሳት፣ ኢሳያስ አፈወርቂ ለሚያከናውኑት የግብረ-ሽበራ ስራ በወሮታው ዶላር ይወረውሩ ገቡ፡፡ ጥገኛው ኢሳያስም ከሽብርተኝነት ጋር በፍቅር ወደቁ፡፡ በንፁሐን ዜጎች ላይም ፈንጂና ቦምብ ሲፈነዳ የማየት ሱስ ተጠናወታቸው፡፡…

በተለይ ሀገራችንን ለማተራመስና ተበታትና ለማየት ካላቸው ጽኑ ፍላጎትም፣ ካኮረፉ ፀረ-ሠላምና ፀረ-ህዝብ ጠባብና ትምክህተኛ ኃይሎች ጀምሮ ሰራ ፍለጋ ከሀገር እስከወጣ ዜጋ ድረስ ማደራጀትና ማስታጠቅን ዋነኛው የመንግስታቸው የድርጊት መርሀ-ግብር አካል አደረጉት፡፡…

ለዚህ እኩይ ተግባራቸውም ሰሞኑን በአሸባሪነት የተሰየሙትን የሀገር ውስጥና የውጭ ቡድኖችን በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ “ትልቁ ለማኝ፡ ለትንሹ ለማኝ ይሰጣል” የሚል ቀመር በማውጣት ይጠቀሙባቸው ገቡ፡፡ ራሳቸውን “ኦነግ”፣ “ኦብነግ”፣ “ግንቦት 7”፣ “አልሸባብ” እና “አልቃኢዳ” እያሉ የሚጠሩ ሽብርተኞች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ሀገራችንን እንዲያሸብሩ በመላክ ያልቆፈሩት ድንጋይ አለ ማለት ዘበት ነው፡፡

ውድ አንባቢዎቼ! ራሱን “ኦነግ” እያለ የሚጠራው የሽብር ቡድን፡ በሽግግር መንግስቱ ምስረታ ወቅት ተሳታፊ የነበረ፣ የተረቀቀውን ቻርተር ፈርሞ ለአንድ ዓመት ያህል ከቆየ በኋላ ሰላማዊ መድረኩን ረግጦ ወደ ሽምቅ ውጊያ የገባ ፀረ-ህዝብ ኃይል መሆኑን ታስታውሳላችሁ፡፡ ታዲያ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በህዝቡ ስለተተፋ ኃይሉ እየተመናመነ በመምጣቱ ወደ ግብረ-ሽበራ ስራ በቀጥታ የተሰማራ አሳፋሪ “ድርጅት” ነው፡፡

የኤርትራ መንግስት የነውጥ ስትራቴጂው ዋነኛ ተላላኪ በመሆንና ጽህፈት ቤቱን አስመራ ላይ ከፍቶ በአሸባሪነት የሚንቀሳቀሰው ይህ ፀረ-ህዝብ ኃይል፣ የኢሳያስ አፈወርቂ “ተወርዋሪ ድንጋይ” ሆኖ ሀገሩንና ህዝቡን በከሃዲነት ሲያተራምስ ቆይቷል፡፡ የሽብር ቡድኑ በሻዕቢያ አይዞህ ባይነት ሀገራችን ውስጥ በቀበሌዎች፣ በመንግስት ተቋማትና ጽህፈት ቤቶች፣ በአገልግሎት መስጫ ተቋማት ወዘተ… ከባቢዎች ላይ ባደረገው የጥፋት ተልዕኮ በ1987 ዓ.ም እስከ 2000 ዓ.ም ድረስ ብቻ 106 የሽብር ጥቃቶችን አድርሷል፡፡ በዚህም 56 ንፁሐን ዜጎችን የገደለ፣ 284 ሰዎች ላይ ከባድና ቀላል የአካል ጉዳት ያደረሰና ከፍተኛ መጠን ያለው ንብረት እንዲወድም ያደረገ ተላላኪ ነው፡፡…

ራሱን “ኦብነግ” እያለ የሚጠራው ድርጅትም፣ ከኤርትራ መንግስት ከፍተኛ ድጋፍ በማግኘት በሀገራችንና በህዝባችን ደህንነት ላይ ያነጣጠሩ በርካታ የሽብር ጥቃቶችን የፈፀመ ቡድን ነው፡፡

ይህ ፀረ-ሠላም ኃይል ከሽግግር መንግስቱ አፈንግጦ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ በሻዕቢያው አስተዳደርና በአልሸባብ ድጋፍ ብሎም የቅርብ ክትትል፣ በንፁሐን ሰዎች፣ በልማት ተቋማትና፣ በበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ንብረቶች ላይ ያነጣጠሩ የአሸባሪነት ተግባራትን ፈጽሟል፡፡

በዚህም ከ1988 ዓ.ም እስከ 2003 ዓ.ም ድረስ ከ132 በላይ ሰዎች እንዲሞቱና ከ54 በላይ ደግሞ ቀላልና ከባድ የአካል ጉዳት እንዲደርስባቸው አድርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም፣ ከ25 በላይ ሰዎችን አፍኖ ወስዷል፡፡

አሸባሪው “ኦብነግ” በተለያዩ ጊዜያት ሽብር ፈፃሚ ሰዎችን ኤርትራ ውስጥ አሰልጥኖና አስታጥቆ ወደ ሀገራችን እንዲገቡ ብሎም የሽብር ጥቃት እንዲያደርጉ ትእዛዝ ሲሰጥና ሲያስፈጽም መቆየቱ የሚታወስ ነው፡፡

በዚህም የኢሳያስ አፈወርቂ  ተላላኪ በመሆን በግንባር ቀደምትነት የግብረ-ሽበራ “ሎሌ” ሆኖ በማገልገል ላይ የሚገኝና ሌላኛው የሻዕቢያ ቅጥረኛ ቡድን ሆኖ የሚንቀሳቀብ ኃይል ነው፡፡

አሸባሪው “ኦብነግ” በተለያዩ ጊዜያት ሽብር ፈፃሚ ሰዎችን ኤርትራ ውስጥ አሰልጥኖና አስታጥቆ ወደ ሀገራችን እንዲገቡ ብሎም የሽብር ጥቃት እንዲያደርጉ ትእዛዝ ሲሰጥና ሲያስፈጽም መቆየቱ የሚታወስ ነው—የተላላኪ ተላላኪ ሆኖ። በዚህም የኢሳያስ አፈወርቂ ተላላኪ በመሆን በግንባር ቀደምትነት የግብረ-ሽበራ ሎሌ ሆኖ በማገልገል ላይ የሚገኝና የሻዕቢያ ቅጥረኛ ቡድን ሆኖ የሚንቀሳቀስ ጥቂት ኃይል ነው፡፡

ይሁንና እርሱም ሆነ ላኪው ሻዕቢያ በኦጋዴን በኩል ያደረጉት የሽብር ተግባር አልቀናቸውም። ምክንያቱም የሽብር ቡድኑ በአሁኑ ወቅት በሶማሌ ክልል ህዝብ “በተለይም ለነፃነቱ ነው የምታገለው” በሚለው የኦጋዴን ህዝብ ይሁንታ በማጣቱና በኢፌዴሪ መከላከያ ሰራዊት በደረሰበት ተደጋጋሚ ወታደራዊ ኪሳራ ኃይል የለሽ ደረጃ ላይ የሚገኝ የጥቂት ግለሰቦች ስብስብ የሆነበት ደረጃ ላይ ስለደረሰ ነው።

ከዚህ ጎን ለጎንም በተለያዩ ጊዜያት አብዛኛው አባሉ የሽብር ቡድኑን እኩይ ሴራ በመገንዘብ ህገ-መንግስቱንና ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱን ተቀብለው ሀገር ውስጥ ሰላማዊ ህይወታቸውን በመምራት ላይ መገኘታቸው ቡድኑን ትርጉም የለሽ እንዲሆን ያደረገው ምክንያት ነው።

በአሁኑ ወቅትም ቢሆን ‘የኢፌዴሪን ህገ-መንግስት በመቀበል ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር ቀጥተኛ ድርድር ማድረግ አለብን’ በሚሉ አባሎቹ እየተናጠ ያለው የተመናመነው የአስመራው “ኦብነግ”፤ በሞት አፋፍ ላይ ቆሞ በጣር ላይ እንዳለ በሽተኛ የሚመሰል ነው።

ዳሩ ግን አቶ ኢሳያስ እንደ “ኦብነግ” ዓይነት ተላላኪዎች የሀገራችንን ሰላም ለማወክ አስፈላጊዎች ስለሚመስሏቸው ቡድኑን “እባክህን ጥለኸኝ አትሂድ” የሚል ጉባኤ አዘጋጅተው ሞቱን በገንዘብ ሃይል ለመግዛት ደፋ ቀና እያሉ ናቸው። ይሁንና የሻዕቢያው ጉባኤ የሽብር ቡድኑን ‘ህገ-መንግስቱን እንቀበል’ ሃሳብ ብዙም የሚቀይረው እንዳልሆነ የፖለቲካ ተንታኞች ይስማሙበታል።

ውጭ በሚኖሩ የቀድሞው የቅንጅት ነውጠኛ አመራሮች፣ አንዳንድ የደርግ ባለስልጣናት እና መኮንኖች የተደራጀውና ራሱን “ግንቦት 7” እያለ የሚጠራው ሽብርተኛ ድርጅትም፣ ከምርጫ 97 በኋላ የተቋቋመ ፀረ-ኢትዮጵያ መንግስት አቋም ካላቸው ሀገሮች ጋር የሚሰራና፣ የሀገራችንን ዴሞክራሲያዊ ህገ-መንግስታዊ ሥርዓት “በማንኛውም መንገድ እናፈርሳለን” በሚል የቅዥት ፖለቲካ የአቶ ኢሳያስ አስተዳደር ተላላኪ በመሆን እያገለገለ ይገኛል፡፡

የሽብር ቡድኑ በየጊዜው አስመራ እየተመላለሰ ከኢሳያስ አፈወርቂ በሚቀበለው መመሪያ መሠረትም በከተማ የመሰረተ-ልማቶችና በከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት ላይ ውድመት፣ ሽብርና ግድያ በመፈፀም ሲያሴር የነበረ ነው፡፡ ይህን ፀረ-ህዝብ ተግባሩን እውን ለማድረግም አባላቱን ኤርትራ በመውሰድ የፈንጂና የግድያ ስልጠና እንዲያገኙ አስደርጓል— ምንም እንኳን ህልሙ እንደ ሌሎቹ ተላላኪዎች መክኖ የቀረ ቢሆንም፡፡…

… ሌላው የሻዕቢያ ጀሌ አልሸባብ ነው፡፡ ይህ የውጭ ሀገር ሽብርተኛ ቡድን በኢሳያስ አፈወርቂ መንግስት በመሳሪያና በገንዘብ አቅርቦት የሚደገፍ ሲሆን፣ ሀገራችን ላይ “ጅሃድ” እስከማወጅ የደረሰ ጽንፈኛ የሶማሊያ ድርጅት መሆኑ ይታወቃል፡፡ በዚህም በሻዕቢያ አይዞህ ባይነት በኢትየጵያ እና በኢትዮጵያውያን ጥቅሞች ላይ የሽብር ጥቃቶችን ሲፈጽም የነበረ ነው፡፡

ከቅርብ ጊዜ ትውስታችን ብንነሳ እንኳን እ.ኤ.አ በጁላይ 2010 ኡጋንዳ-ካምፓላ ውስጥ 19ኛውን የዓለም ዋንጫ የፍፃሜ ጨዋታን “የኢትዮጵያውያን መንደር” ተብሎ በሚታወቀው መዝናኛ ማዕከል በመከታተል ላይ ባሉ ሰዎች ያደረሰው የፈንጂ የሽብር ጥቃት ተጠቃሽ ነው፡፡

ይህ ከአልቃኢዳ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት እንዳለው የሚገለፀው የሽብር ቡድን፣ በወቅቱ ካምፓላ ላይ የፈነዳው ሲ-4 የተባለ ፈንጂ፣ “አዲስ አበባን እንደ ባግዳድ” በተሰኘው ዘጋቢ ፊልም ላይ የኦነግ አሸባሪዎች 16ኛውን የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባዔን ለማወክ ተዘጋጅቶ ከነበረውና በቁጥጥር ሥር ከዋለው ፈንጂ ጋር ተመሳሳይነት ያለው መሆኑ ቀጣዩን እውነታን ፍንትው አድርጐ ያሳየናል፡፡

እነዚህ የሻዕቢያ ድርጊቶች ጠቅለል ተደርገው ሲታዩ የአስመራው ቡድን መቼም ቢሆን የሽብር እጆቹን የሚሰበስብ አለመሆኑን ነው። የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽነር ጄኔራል አሰፋ አብዩ፣ ምርጫ ሲሰማ የሚያስደነግጠው የአሰመራው ቡድን የሚያካሂደው ትንኮሳ ለዚህ ሁነኛ ማረጋገጫ ነው። እናም ይህ የግብረ-ሽበራ ፊታውራሪ ቡድን ሁከትን እንደ እድሜ ማራዘሚያ እንክብል መድሃኒት የሚመለከት በመሆኑ እያናወነ ለሚገኘው ተግባር ተመጣጣኝ እርምጃ ሊወሰድበት ይገባል ባይ ነኝ።